# ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ

# የወጣ መመሪያ

*የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን*

*ነሐሴ 2001 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ*

# ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ

# የወጣ መመሪያ ቁጥር 25/2001

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 16 መሠረት በተመዘገቡና ባልተመዘገቡት መካከል የሚፈጠረውን ተገቢ ያልሆነ የገበያ ውድድር መልክ ማስያዝና ከየዘርፉ ተገቢውን ታክስ መሰብሰብ ስለሚገባ፣

ድርጅቶች በቅርንጫፎቻቸው በሚያከናውኑት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ በአንድነት አስልቶ ለመክፈል በሚያስቸግራቸው ጊዜ በተናጠል እንዲመዘገቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተናጠል ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ መሟላት ስለሚገባው ቅድመ ሁኔታና መከናወን ስላለበት ተግባር ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 16(6)፣ አንቀጽ 18(1) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 አንቀጽ 39 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. *አጭር ርዕስ*

ይህ መመሪያ "ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ስለመመዝገብ የወጣ መመሪያ ቁጥር 25/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. *ትርጓሜ*

**ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም**

1. ***"ማንኛውም ሰው"*** ማለት ግለሰብ ነጋዴ፣ ኩባንያ፣ የኅብረት ሽርክና ማኅበር፣ የውርስ ወይም የባለአደራ ንብረት አስተዳዳሪ፣ የሕግ ሰውነት

ቢሰጠውም ባይሰጠውም ማንኛውም የንግድ ድርጅት፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት፣ የስፖርት ክለብ ወይም ማኅበር ነው፡፡

2. ***"ግንኙነት ያላቸው ሰዎች"*** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(13) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
3. ***"ግብይት"*** ማለት በአዋጁ  አንቀጽ 2(22) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡
4. ***"ሽያጭ"*** ማለት ማናቸውም ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሲሆን የእቃ አቅርቦትንና አልግሎት መስጠትን የሚጨምር ነው፡፡
5. ***"መኖሪያ"*** ወይም ***"ማረፊያ ቦታ"*** ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ፣ ወይም በማዘውተር በማረፊያነት የሚጠቀሙበት ቦታ ነው፡፡
6. ***"አዋጅ"*** ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 ነው፡፡
7. ***"ደንብ"*** ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 79/1995 ነው፡፡
8. ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፡፡
9. ***"ዋና ዳይሬክተር"*** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

## 3. *ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት በግዴታ ወይም በፈቃደኝነት ስለመመዝገብ*

1) ማንኛውም ሰው የተጨማሪ እሴት ታክሱ ሳይታከልና ከታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶቹ በአጠቃላይ ዓመታዊ ሽያጭ ውስጥ ሳይደመሩ የ12 ወራት ጥቅል ሽያጩ ከብር 500,000 የሚበልጥ ወይም እንደሚበልጥ ለመገመት የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት ያለ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተመለከተው የሽያጭ መጠን ገደብ ቢኖርም በማናቸውም ተከታታይ 12 ወራት ጊዜ ውስጥ ሽያጩን ቢያንስ 75% ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ ሰዎች የሚያቀርብ ከሆነ ዓመታዊ ሽያጩ ብር 500,000 ባይሞላም በፈቃደኝነት መመዝገብ ይችላል፡፡

3) በግዴታም ሆነ በፈቃደኝነት የሚፈፀመው የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ምዝገባ ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው “የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ማመልከቻ” ፎርም ወይም ቅጽ መሠረት መሆን አለበት፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ቢኖርም ምዝገባ ጠያቂው ቋሚ የመኖሪያ ወይም /የማረፊያ ቦታ ወይም የንግድ ሥራ የሌለው ወይም ተቀባይነት ያለው የሂሣብ መዝገብ የማይዝ ከሆነ ወይም የባንክ ሂሣብ ከሌለው ባለሥልጣኑ ምዝገባውን ላይቀበል ይችላል፡፡

## 4. በግዴታ ስለመመዝገብ

1) ከዚህ በላይ በአንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሆኖ ያልተመዘገበን ሰው ባለሥልጣኑ በራሱ ጊዜ በመመዝገብ የምዝገባ ሰርተፊኬት መስጠት እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (6) ላይ ተመልክቷል፡፡

2) አንዳንድ የንግድ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከዘርፉ የንግድ እንቅስቃሴ ባህሪ አንፃር ዓመታዊ ሽያጫቸው ለግዴታ ምዝገባ የሚያበቃቸው ሆኖ ቀርበው ካልተመዘገቡ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 18(6) መሠረት እንዲመዘገቡ በማድረግ ሕጉን ያስፈጽማል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተውን መነሻ በማድረግ

ሀ/ ከፍተኛ የንግድ እቃዎች ዋጋ በያዙ የንግድ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩ፣

ለ/ ከፍተኛ የገበያ ጥያቄ ያላቸውን እቃዎች ግብይት የሚያካሂዱ፣

ሐ/ የተሰማሩበት የማምረት ሥራ የሚጠይቀው የካፒታል መጠንና የምርት ውጤት ከፍተኛ የሆኑ የንግድ ዘርፎች ውስጥ፡-

- ☞ ወርቅ ቤቶች፣
- ☞ ኤሌክትሮኒክስ ንግድ /በተለይ ፍሪጅ፣ ዴክ፣ ሞባይል፣ ቴፕ እና ቴሌቪዥን ሽያጭ ላይ የተሰማሩ/፣
- ☞ አስመጪዎች፣
- ☞ ኘላስቲክና የኘላስቲክ ውጤቶች አምራች ፋብሪካዎች፣
- ☞ ጫማ ፋብሪካዎች፣
- ☞ ከደረጃ 10 በላይ /1-9/ ያሉ ሥራ ተቋራጮች /ኮንትራክተሮች/፣

☞ ኮምፒዩተርና የኮምፒዩተር መለዋወጫ መሸጫ መደብሮች፣

☞ ቆዳና የቆዳ ውጤቶች /በተለይ የቆዳ አምራቾች፣ ከቆዳ የሚሰሩ አልባሳት ወይም ቦርሳዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚሸጡ/

ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው፡፡

4) ሌሎች የሥራ ዘርፎችም እየተጠኑ ባለሥልጣኑ በሚያስተላልፈው ሰርኩላር ወይም በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ይመዘገባሉ፡፡

## *5. ግንኙነት ያላቸውን ሰዎች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ*

ባለሥልጣኑ ሁለት ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በየግል የሚያከናውኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ብር 500,000 ባይሞላም አንዱ ያከናወነውን ግብይት ሌላው ካከናወነው ጋር በመደመር ሁለቱም በየግላቸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት እንዲመዘገቡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## *6. ከአንድ በላይ የሆኑ ቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች በተናጠል ስለሚመዘገቡበት ሁኔታ፣*

1) በአዋጁ አንቀጽ 16(4) ላይ እንደተመለከተው ቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች መመዝገብ ያለባቸው በዋናው ተመዝጋቢ ስም ቢሆንም ቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች በተናጠል እንዲመዘገቡለት ጥያቄ ከቀረበ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችንና ገደቦችን በማስቀመጥ የተናጠል ምዝገባውን መፍቀድ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ (5) እና (6) ላይ ተመልክቷል፡፡

2) በተናጠል ለመመዝገብ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦችን በተመለከተ በደንቡ አንቀጽ 9 ሥር ከተደነገጉት በተጨማሪ የሚከተሉት ሁኔታዎች በዋናነት ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

ሀ/ ዋናው መስሪያ ቤት ቅርንጫፎች ወይም የሥራ ክፍሎች በተናጠል እንዲመዘገቡለት የተናጠል ምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ለ/ ቅርንጫፎቹ ወይም የሥራ ክፍሎቹ ራሱን የቻለ የሂሣብ አያያዝ ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ሐ/ ዋናው መሥሪያ ቤት ቅርንጫፎቹ ወይም የሥራ ክፍሎቹ ሁሉ እንደአንድ ድርጅት መመዝገባቸው የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብም ሆነ በሌሎች የታክስ ግዴታውን በመፈፀም ረገድ ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትልበት መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት አለበት፡፡

መ/ የቅርንጫፎቹ የንግድ ሥራ ዓይነት ወይም ዘርፍ የተለያየ መሆን እና በዚህም ተለይተው የሚታወቁ መሆን አለባቸው፡፡

ሠ/ የቅርንጫፎቹ ወይም የሥራ ክፍሎቹ የሥራ አድራሻም ተለይቶ የሚታወቅና ማረጋገጫ የሚቀርብበት መሆን አለበት፡፡

ረ/ ቅርንጫፎቹ ወይም የሥራ ክፍሎቹ ከዋናው መስሪያ ቤታቸው ያላቸው ርቀት <u>ከ100</u> ኪ.ሜትር በላይ መሆን አለበት፡፡

ሰ/ ለየቅርንጫፎቹ ወይም ለየሥራ ክፍሎቹ የሚሰጠው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር ለዋናው መስሪያ ቤታቸው የተሰጠው ሆኖ ቅርንጫፎቹን ወይም የሥራ ክፍሎቹን ለመለየት እንዲቻል በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የተለየ ምልክት ሊኖረው ይገባል፡፡

ሸ/ የተናጠል ምዝገባ የሚከናወነው ባለስልጣኑ ሲፈቅድ ብቻ በመሆኑ በተለይ በደንቡ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (9) ሥር የተመለከቱት ተሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

ቀ/ ባለሥልጣኑ የተናጠል ምዝገባ ጥያቄውን ከማጽደቁ በፊት በዚህ መመሪያም ሆነ በደንቡ ከተዘረዘሩት ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም በተለያዩ ክልሎች የንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት የሚሠራ ግለሰብ ነጋዴ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት በዋና ተመዝጋቢ ሥም በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የዋና ንግድ ምዝገባ ባከናወነበት አንድ ቦታ ብቻ ነው፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተመለከተው መሠረት በአንድ ቦታ የተመዘገበ ሰው በብዙ ክልሎች የንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት ሲሰራ ዋናው

የንግድ ምዝገባ መዝገብ እየተጠቀሰ በአጭር ቃል እንደሚመዘገብ ሁሉ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባም በዋናው ምዝገባ ቦታ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ሲመዘገብ የተሰጠው የምዝገባ ቁጥር ብቻ እየተጠቀሰ መመዝገብና ሂሣቡን በማስታወቅ መክፈል ይኖርበታል፡፡

## 7. *<u>የሃይማኖት ድርጅቶች ተነጣጥለው ስለሚመዘገቡበት ሁኔታ</u>*

1) የሃይማኖት ድርጅት ከአምልኮት ጋር በተያያዘ ከሚሰጠው አገልግሎት ውጪ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶችን የሚያካሂድ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ያለበት መሆኑ የሚወሰነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ጠቅላላ እንቅስቃሴ ተደምሮ ነው፡፡
2) የሃይማኖት ድርጅቱ በሚያከናውነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ በአንድነት አስልቶ በእያንዳንዱ የሂሣብ ጊዜ አንድ የታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ የሚያስቸግረው መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን የተረዳ እንደሆነ የሃይማኖት ድርጅቱ የተለያዩ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ጥያቄ ሲያቀርብ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
3) ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያለበት የሃይማኖት ድርጅት በሥሩ ያሉት የልማት ተቋማት ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ቅርንጫፎች ተነጣጥለው እንዲመዘገቡ ለባለሥልጣኑ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ በዚህ ዓይነት በተናጠል ምዝገባ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ሙሉ ሥልጣን አለው፡፡
4) የሃይማኖት ድርጅት ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ የቀረበውን ጥያቄ ባለሥልጣኑ የተቀበለው ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት የሃይማኖት ድርጅቱ የልማት ድርጅቶች ወይም ተመሳሳይ ተግባር ያላቸው አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቅርንጫፎች በተናጠል እንዲመዘገቡ ያደረገ እንደሆነ፣ የተናጠል ምዝገባ የሚከናወነው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ሥር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ወይም ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን ሁኔታ እና ገደብ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

5) የሃይማኖት ድርጅቶች በሥራቸው ያሉ ድርጅቶች በአንድነትም ሆነ በተናጠል ምዝገባ የሚከናወነው በባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ስለሆነ የሚመለከታቸው ቅርንጫፎችና የሥራ ሂደቶች ተከታትለው ሕጉን ማስፈፀም አለባቸው፡፡

## 8. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመጽደቁ በፊት ተጀምረው የነበሩ ሥራዎች በተጀመሩበት ሁኔታና በነበረው መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

## 9. የተሻሩ መመሪያዎች

ከምዝገባ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል ወጥተው የነበሩ መመሪያዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

## 10. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋና ዳይሬክተሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ --------------- ቀን 2001 ዓ.ም.

መላኩ ፈንታ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ዋና ዳይሬክተር